# የልዕለ -ሀያላን ሽግሽግና የመስመራችን ብቃት!!

*ዓለማየሁ ሞገስ 11-27-17*

እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ከ1980ዎቹ በኋላ በአለም በርካታ ሀገሮች ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ይዞታቸው ለውጥ እየታየበት ስለመምጣቱ የምጣኔ ሀብትና የፖለቲካ ምሁራን ትንተናዎች ፤ ከታሪክና የኣለማቀፍ መገናኛ ብዙንን ከሰጡት ሽፋን ተነስተን የምንለው ይኖራል፡፡ እነዚሁ የመረጃ ምንጮቹ ለየሀገሮቹ አስገራሚ የፖለቲካ ፤ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ይዞታ ለውጥ ምክንያት ይሆናሉ ከሚሏቸው በርካታ ማሳያዎች መካከል ሁለቱን በዋናነት ብጠቅስ የነገሩን-ፍሬ ምዕሉነት አያጓድልም ብየ አሰብሁ፡፡

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ በኋላ በፈረንጆች (1990) መጀመሪያ በመላው አለም የአምባ ገነን መንግስታት ከበትረ መንግስታቸው በሀይል ከስልጣን መገርሰስና በምትክቸው የነፃ ገበያ ስርዓትና ዲሞክራቲክ አስተሳሰብ በሚያራምዱ መንግስታት እየተተኩ መሄድ፤ ይህንኑ ተከትሎ ፤ ከማዕከላዊ መንግስት አወቃቀር ወደ ነፃ የገበያ ስርዓት የሚደረገው ሽግግር እየጠነከረ መምጣትና ፤ የማታ ማታም በምትኩ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ መፋፋት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ( Charles W.L. Hill Global Business Today,2006).

እንደ ፖለቲካል ኢኮኖሚስቶች ትንታኔ የዕዝ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ሀብት በማውደም ወይም በመቀራመት ላይ የተመሰረተ ስርዓት ነበር ፡፡ ማህበረሰቡን የተሻለ የማምረት አቅም ፈጥሮ በነበረው ጥሪት ላይ አዳዲስ ሀብት የመፍጠር አማራጭ አይከተልም፡፡ የዕዝ ኢኮኖሚ በስርዓቱ ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ መንግስት በሚሆንበት ጊዜ የሀብት ክፍፍሉ ፍትሀዊነት በሌለበት ሀገር መንግስት ዋናው የኢኮኖሚ ተዋናይ በማድረግ በፍትሀዊነት ለህዝቡ ማከፋፈል ይቻላል ከሚል ጽንሰ ሀሳብ የሚነሳ ነው፡፡

በእንዲህ ዓይነቱ የኢኮኖሚ ስርዓት አስተሰሰብ መንግስትን በዋና ዋና የኢኮኖሚ ሴክተሮች ብቻ ሳይወሰን ፤ በግል ባለሀብቱ ሊሸፈን የሚችልባቸውን የኢኮኖሚ ሴክተሮች ጨምሮ ያቅዳል ይወስናል ፡፡ የችርቻሮና የጉልት ስራ ሳይቀር ገደብ በሌለው ጣልቃ ገብነት ይቆጣጠራል፡፡

ስርዓቱ በተግባር እንደተረጋገጠው ዜጎች በራሳቸው ተነሳሽነትና የፈጠራ አቅም ተጠቅመው ሀገራቸውን በኢኮነኖሚ ለማሳደግ የሚያደርጉትን ጥረት በእጅጉ ይገድባል፡፡ ለአንድ ሀገር ልማት ዜጎች በአምራች እንቅስቃሴ ዘርፍ ተሰልፈው ሊያበረክቱት የሚገባውን ተነሳሽነት ይነፍጋል፡፡

ስርዓቱ በ2ኛው ሚሊኒየም ማጠናቀቂያ በምስራቅ አውሮፓ ሀገሮች በዩጎዝላቪያ፤ ሮማኒያ ፣ በዩክሬን፣በቀድሞዋ ሶቭት ህብረት ፤ በአፍሪካ ሀገሮችም በኢትዮጲያ ፤ በዚምባዌ፤ በሊቢያ ተሞክሮ ስሬ ህዝባዊ ተቃውሞ ደርሶበታል፡፡ በሀገራችን ኢትዮጲያም በርካታ አብዮታዊ ሀይሎች ወደ ትጥቅ ትግል እንዲገቡ ምክንያት ሆኗል ፡፡

የዕዝ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ተጠያቂነት የሌለበት የመንግስት ስልጣንና ሀይል በጥቂቶች እጅ ወድቆ ትርጉም ያለው ማህበረሰባዊ ህይወት መሻሻል ሳያስመዘግብ ፤ ይልቁንም ሙስና፤ ኪራይ ሰብሳቢነትና ጸረ- ዲሞክራሲያዊነት ተባብረው በዝረራ ከገበያ ውጭ አድርገውታል፡፡ በዕዝ ኢኮኖሚ ተቀፍድዶ የቆየው የሶሻሊስት ስርዓት መፍረክረክ ለሶቬየት ህብረት መበታተንና የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያን አስከተለ ፡፡

ከዚህ ታሪካዊና ዓለማቀፋዊ ክስተት በኋላ ደግሞ የዓለም ሀገሮች ከሌላ ሞጋች ሁኔታ ጋር ተፋጠጡ፡፡ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር 1989 ሊበራል የፖለቲካል ኢኮኖሚ ዓለማቀፋዊ ቅርፅ ይዞ ብቅ አለ፡፡ ይህ ክስተት የመድብለ ፓርቲና የነጻ ገበያ የኢኮኖሚ ስርዓት ሽታ ዓለምን እንዲያውድ ምክንያት ሆኗል ፡፡

ሊበራል የገበያ ስርዓት በማናለብኝነት ስሜት መላው አለም ሳይወድ በግድ በዚህ ስርዓት እንዲጠመቅ ተደረገ ፡፡ በሶቪዮት መፈረካከስ ማግስት የሊበራል ፖለቲካል ኢኮኖሚ የአሸናፊነት መንፈስ ፅንፍ ከረገጡ አፍቃሪ ሊበራል ኢኮኖሚስቶችና በራሱ አካል አምሳል የፈጠራቸው ሊበራል ሚዲያዎች ታግዞ ነጻ የገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት አማራጭና የተለያየ መልክ ይዞ መጣ፡፡ የፈረንሳይ ፤ የስዊድን ፤ የአሜሪካ፤ የጀርመን ካፒታሊዝም እያልን ልናያቸው እንችላለን፡፡

የሊበራል የገበያ አማራጭ በባህሪው የነጻ ገበያ ስርዓት አማራጭ ነው፡፡ ኒዮ ሊበራል አዲሱ ሊበራል ልንለው እንችላለን፡፡ በአዲሱና አሮጌው ሊበራል መካከል ያለውን አማራጭ ለማየት ከ1978 እ. ኤ. አ በኋላና በፊት ያለው የስርዓቱ ገፅታ ማየት ብቻ በቂ ነው፡፡

አሮጌው ሊበራሊዝም በ17ኛው ክ/ዘመን የተጀመረ ሲሆን ዋነኛ ይዘቱ ለባለሀብቱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር በሚል የተጀመረ አስተሳሰብ ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሞከረው በ1975 በቺሊ በኋላም በአሜሪካና እንግሊዝ ፈረንሳይ እያለ ተስፋፍቷል፡፡

መነሻው የአውሮፓ ፊውዳሎች ያመረቱትን ምርት ወደ ኢንደስትሪ ምርት በመቀየር በገበያ የመሸጥ አጀንዳ ነበር፡፡ ይህ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ ለመሸጥና የባለሀብቱን ጥቅም ወደ ፊት ለማስቀጠል የተጀመረ ስርዓት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ፊውዳሊዝምን አስወግዶ የመንግስት ቁጥጥር ያልተለየው የነፃ ውድድር ስርዓት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ይህ አስተሳሰብ እስከ አንደኛው የአለም ጦርነት ድረስ ቀጥሏል፡፡

ኒዮ -ሊበራሊዝም አዲሱ ሊበራሊዝም እንደ ማለት ነው፡፡ መንግስት ህግ ከማውጣት ባለፈ በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም ፡፡ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ እጁን የሚያስገባ ከሆነ የባለሀብቱን አቅም ያዳክማል ከሚል አስተሳሰብ የሚነሳ የኢኮኖሚ እሳቤ ነው፡፡

ኒዮ- ሊበራሊዝም ከ1978 እ.አ.አ ጀምሮ በአለም ኢኮኖሚ ቁልፍ ቦታ ባላቸው አሜሪካና እንግሊዝ የበላይነት ይዞ ቀጥሏል፡፡ እነዚሁ ሀገሮች ስርዓቱን የአለም ባንክና የአለም የገንዘብ ድርጅትን የፖሊሲ ማስፈጸሚያ በማድረግ እስከ ቅርብ ጊዜም ቢሆን ያለ ተፎካካሪ በመላ አለም እንዲናኝ አድርገውታል፡፡ ወደ አፍሪካ የመጣውም በዚሁ መንገድ እንደ አውሮፓውያኖች አቆጣጠር ከ1978 በኋላ ነው፡፡

አፍሪካውያን ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ከወጡ ከ 1960 በኃላ የኣለማችን ሀገሮች ወይ በዕዝ አልያም ደግሞ በካፒታሊስት ስርዓት በመወገን አለም በሁለት ጎራ የተከፈለች ሆና እንድትቆይ ተደርጓል፡፡

የአፍሪካ ሀገሮችም ከሞላ ጎደል ከቅኝ ገዥዎቻቸው የተረፈችዋን ሀብት ይዘው በመንግስታዊ ቁጥጥር /ሶሻል ዲሞክራሲን/ አልያም ደግሞ የካፒታሊስት ስርዓትን ተቀብለው መንገዳገድ ጀምረው ነበር፡፡ ለነገሩ አፍሪካ ከቀኝ ገዥዎቻቸው ከኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ አመለካከት በስተቀር ለልማት መነሻ የሚሆን ቅንጣት ያህል የመሰረተ ልማት አውታር ሳይዘረጉ ነው የቆዩት፡፡

በዚህም ምክንያት ከቅኝ ግዛት በኋላ የማምረትና ትርፍ ሀብት የማከማቸት አቅማቸው እጅግ ውስን ሆነ፡፡ አለ የሌለ መተማመኛቸውም የተፈጥሮ ሀብት ፤ ነዳጅ ወዘተ.. ባሻገር የግብርና ምርት ነበር ፡፡ የአፍሪካ ሀገሮች ባለፉት የቅኝ ግዛት ዘመናት የመንግስት ወጭያቸው እየጨመረ የማምረት አቅማቸው እጅግ እየቀነሰና እያሽቆለቆለ ራሳቸውን ሳይችሉ በሄዱ ቁጥር በቅድመ ሁኔታዎች ለሚሰጠው አለም ባንክና አይኤምኤፍ ብድርና እርዳታ ተጋልጠው ቆይተዋል፡፡

ከኒዮ-ሊበራሊዝም ሁለት ማጠንጠኛዎች መካከል አንዱ ሁሉንም ነገር ለባለሀብቱና ገበያው መተው ፤ ሲሆን ሌላኛው የአፍሪካ መንግስታት የሙስናና ኪራይ ሰብሳቢ መዋቅሮች ናቸው ብሎ መደምደሙ ነው፡፡ እነዚህን ሁለት ማደማደሚያዎች በመያዝ የአፍሪካ መንግስታት በጎሳ፤ በዘር፤ የተሰባሰበ የዝርፊያ መረቦች ስለሆኑ ህግ ከማውጣትና ከማስከበር ባለፈ በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ መግባት አይጠበቅባቸውም ብሎ ይሞግታል፡፡

በዚህም ምክንያት ስትራክቸራል አድጀስትመንት/ ፕራይቬታይዜሽን / በሚል የማስፈፀሚያ ስልት ለከተማ ህዝብ የሚቀርበው ንፁህ የመጠጥ ውሃ ሳይቀር ፤ የቴሌኮሙኒኬሽን፤ የመብራትና የባንክ ተቋማት ጨምሮ ወደ ባለሀብቱ መዞር አለባቸው የሚሉ አስገዳጅ የፖሊሲ ጫናዎችን ጥሏል፡፡ ኒዮ-ሊበራሊዝም፡፡ የነፃ ገበያ ካፒታሉ ምረታማነትን በመጨመር የሚመጣ ሳይሆን የህዝብ ተቋማትን የህዝብ አንጡራ ሀብትን ወደ ግል ይዞታ በማዛውር የህዝብ ንብረት ዝርፊያ ስትራተጅ ሆኖ በተግባር ታይቷል፡፡ የህዝብ መጠቀሚያን ሀብት ወደ ግል ይዞታ በማዛወር ረገድ በዋናነት እያስፈፀሙ የሚገኙትም የአለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት ናቸው፡፡

በዚህ ምክንያት የአፍሪካ ታዳጊ ኢንደስትሪ ከቅኝ ግዛት ማግስት ገና ከጅምሩ እንዲቀጭጭ ብቻ ሳይሆን እንዲመክን ተደርጓል ፡፡ የወለድ ምጣኔ ፤ የውጭ ምንዛሬ ተመን፤ የመሳሰሉት የማክሮ ኢኮኖሚ አመላካቾች አለመረጋጋት፤ በፕራይቬታይዜሽን ስም የህዝብን ሀብት ወደ ግል ይዞታ ማዛወር የፈጠራቸው ችግሮች ናቸው ፡፡

ገበያ አክራሪ የኢኮኖሚ ስርዓት በአፍሪካ የተስፋፋው የአፍሪካ መሪዎች ሙሰኞችና ኪራይ ሰብሳቢዎች በመሆናቸው ትልቅ መሆን የለባቸውም ጡንቻ ሊያወጡ አይገባም የሚል ጫፍ የረገጠ ማደማደሚያ በመስበክ ነው፡፡ የአፍሪካ መሪዎች ሌቦችና ጉቦኞች ስለሆኑ በኢኮኖሚው ውስጥ በተመረጠ መንገድም ቢሆን ጣልቃ መግባት የለባቸውም ብለው ታሳቢ ያደርጋሉ፡፡

የአፍሪካ መሪዎች ኪራይ ሰብሳቢና ሙሰኛ ናቸው የሚለው ግምገማ የሚያከራክር ባይሆንም ፣ ትልቅና ጠንካራ መንግስት መሆን የለባቸውም !! የሚለው ማደማደሚያ ግን ትክክለኛ መላምት አልነበረም፡፡ በበቂ ትንተና ላይ የተመሰረተ ማደማደሚያ አይደለም፡፡ ምክንያቱም መንግስት ኪራይ ሰብሳቢ የሚሆነው ትልቅ ስለሆነ ፣ ሳይሆን ትንንሽ መንግስታትም በተግባር እንደሚታየው ለኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና ተግባር የተጋለጡ ሆነው እናያቸዋለን፡፡ ለምሳሌ ሶማሌ ፤ ደቡብ ሱዳን ወዘተ...

በተግባር እንደተፈተሸው ዋናው የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ የመንግስታት ትልቅ ወይም ትንሽ መሆን ሳይሆን የመንግስታት የራሳቸው ባህሪ ይሆናል ማለት ነው፡፡ አንድን መንግስት ኪራይ ሰብሳቢ ወይም ልማታዊ የሚያደርገው ትንሽነቱ ወይም ግዙፍነቱ ሳይሆን ባህሪው ነው፡፡ የመንግስታት ባህሪም የሚቀረፀው በሚከተሉት ርዕዮተ -ዓለምና በቆሙለት ማህበራዊ

መሰረት ነው፡፡ ይህን አባባል በራሳቸው በኒዮ-ሊበራሎች ማህበራዊ መሰረት ላይ ተንተርሰን በማስረጃ ማስደገፍ ተገቢነት አለው፡፡

ኒዮ-ሊበራሊዝም ማህበራዊ መሰረቱ የከፍተኛ ምሁራንና የባለሀብቱ አስተሳሰብ ነው፡፡ ማህበራዊ መሰረት ስንል ለጥቅሙ የቆመለት የህበረተሰብ ክፍል ማለታችን ነው፡፡ ኢኮኖሚው ለባለሀብቱ ልቅ የሆነ ወይም ቁጥጥር የሌለበት ፤ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ህግ ከማውጣትና የዘበኝነት ተግባር ውጭ ምንም ሚና እንዳይኖረው የሚያስገድድ ነው፡፡

የኒዮ-ሊበራል የፖለቲካል ኢኮኖሚ ፍልስፍና የገበያ የበላይነት የሚረጋገጠው በውድድር ብቻና ብቻ ነው፡፡ በነፃ ገበያው ለመወዳደር አቅም የሌላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች፤ ዞር ብሎ የሚያይ አይደለም፡፡ በአቅም እጥረትና በኪራይ ሰብሳቢነት አካሄድ ለሚፈጠር የገበያ ክፍተትን ገበያው ይፍታው ብሎ እጁን አጣጥፎ ከመቀመጥ ባለፈ በተመረጠ መንገድ በኢኮኖሚው ጣልቃ ገብቶ የአገልግሎትና ምርት ዕረትን በጥንቃቄ አይፈታም፡፡

በዚህም ምክንያት በነፃ-ገበያ ኢኮኖሚው ለመወዳደር አቅም ያለቸውንና የኪራይ ሰብሳቢነት መንገድ ተከትለው የሚበለፅጉትን ጥቂቶችን የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ ጥቅም ያስጠብቃል፡፡ እነኚህም የህብረተሰብ ክፍሎች ከህዝቡ አንድ በመቶ የሚሆኑት ጥቂት ባለሀብቶችና ምሁራን ናቸው፡፡

ኒዮ -ሊበራሊዝም ፖለቲካል ኢኮኖሚ በተግባርም ያረጋገጠው መንግስት የኢኮኖሚውን ጉድለት ገበያ ይፈታው በሚል እጅ እግሩን አጣጥፎ በመቀመጡ አንድም በነፃ-ገበያው የመወዳደር አቅም ያላቸውን አልያም ደግሞ በኪራይ ሰብሳቢ ፖለቲካል አኮኖሚ በአቋራጭ ወደ ብልፅግና የሚጓዙትን ጥቂት ባለሀብቶችና

የምሁራን ጥቅም ብቻ ያስጠብቃል ፡፡ የማታ ማታም ይህ መላ ምት ኢኮኖሚውን ለቀውስ ህብረተሰቡንም ወደ ጎዳና ወጥቶ የተቃውሞ ድምጹን እንዲያሰማ አስገድዶታል፡፡

የኒዮ -ሊበራሊዝም ፖለቲካል ኢኮኖሚ አስተሳሰብ የተግባር ጉዞ የሚያሳየን ዲሞክራሲ -የብዙሀን እና ለብዙሀን !! ከሚለው ምሁራዊ ትንታኔም ጋር ይጣረሳል፡፡ የብዙሀንን ተጠቃሚነትና የመወሰን ስልጣንም ይገድባል ፡፡ ለደሀና ታዳጊ አገሮች ሳይቀር ዴሞክራሲ ኤክስፖርት እናደርጋለን የሚሎት ታላላቅ ሀገሮች የዴሞክራሲ ስርዓት አተገባበራቸው ጥያቄ ላይ እንደጣለው የበርካታ ምሁራን ጥናቶች ይመሰክራሉ፡፡

ዲሞክራሲ ማለት ብዙሀኑን የመወሰን ፤ስልጣን የመስጠት መብት የሚሰጥ ሆኖ እያለ ኒዮ-ሊበራልና ዲሞክራሲ የሚባሉ የሁለቱ ጋብቻ እንዴት ሊጣጣም ይችላል ? የሚል ሞጋች ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ ጥያቄው ለሰፊ ውይይትና ክርክር የሚጋብዝ በተጨባጭ በሚተነተኑ ማስረጃዎች ማስደገፍ የሚቻል ቢሆንም በዚህ አጭር ፅሁፍ ለውይይት መነሻ ሀሳብ መሰንዘር ከተቻለ በቂ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

በርካታ የፖለቲካ ሳይንስና የምጣኔ ሀብት ምሁራን የዴሞክራሲና የሊበራል ኢኮኖሚ ጋብቻ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ወዲህ የተፈፀመ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ በታላላቆቹ የሊበራል ካፒታል አራማጆች በተለይም አሜሪካና እንግሊዝ ዲሞክራሲ ጥቂቶችን ለማገልገል የተለጠፈ ቅጥያ እንጅ የብዙሀኑን ጥቅም ለማስጠበቅና ለማረጋገጥ ታስቦበት እየተሰራ ላለመሆኑ እነኚሁ ምሁራን ጨምረው ያስረዳሉ፡፡

በነዚህ ሀገሮች ዲሞክራሲ ዘግይቶ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ከ 1978 ዓ.ም ጀምሮ የተደረበ የኒዮ -ሊብራሊዝም የውሸት ካፖርት እንጅ ትክክለኛ ትርጓሜ ይዞ እየተሰራበት እንዳልሆነ ከ2008 ጀምሮ የተከሰተውን የፋይናንስና ኢኮኖሚ ቀውስ ተከትሎ '' ወል ስትሪትን እንቆጣጠር !!'' ፤ '' እኛ ዘጠና ዘጠኝ ከመቶ ነን !!'' የመሳሰሉት ህዝባዊ ተቃውሞዎች ባልታዩ ነበር ፣ ባይ ናቸው ::

ኒዮ ሊበራሊዝም በቅኝ ግዛት በኋላ በአፍሪካ ከፍተኛ የኢኮኖሚ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ በማድረስ የታወቀ ሲሆን የአፍሪካንና ላቲን አሜሪካን ያህል ጫናው ባይነፃፀርም በአውሮፓ ጥቂት የማይባሉ ሀገር ህዝቦች የዚሁ የካፒታል ሲስተም ተጠቂ ነበሩ፤ ናቸውም ::

ኒዮ -ሊበራሊዝም እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ከ2008 ጀምሮ ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ይግባ እንጅ ፣ ቀደም ሲልም ምልዓተ ህዝብን ያሳተፈና በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ ልማት እያስመዘገበ እንዳልሆነ በርካታ ምሁራን (የኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ምሁር የሆኑት ፕሮፌሰር ጆሴፍ ስቲግሊትዝን ጨምሮ ሌሎቹም...) ይስማማሉ፡፡

በያሌ ዩኒቨርስቲ የአለማቀፍ ግንኙነትና ግሎባል ፖለቲክሰ መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር ኢማኑኤል ካፒታሊዝም እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1978 ራሱን ጫፍ በረገጠ የገበያ አክራሪነት ወደ ኒዮ ሊበራሊዝም መቀየሩን ጠቅሰው፣ ስርዓቱ ፍትሀዊ ባልሆነ የሀብት ክፍፍልና በድንበር ዘለል የገበያ ተስፋፊነቱ የሚታወቅ ነው ይላሉ፡፡ ፕሮፌሰሩ አክለውም ስርዓቱ በዓለም በፍጥነት እየታየ ባለው የፖለቲካና ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥም ሆነ በሌሎች ታሪካዊ ምክንያቶች ማህበራዊ ተቀባይነቱም ሆነ ህልውናው ሊያከትም እንደሚችል ምሁራዊ ምልከታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

ያለፉት 30 አና 40 አመታት  ከኒዮ ሊበራል የገበያ ስርዓት በተቃራኒ የልማታዊ መንግስት ስርዓት የተከተሉ የደቡብና ደቡብ ኤሽያ ( ጃፓን ፤ደቡብ ኮሪያ ፤ታያዋን፤  ሆንግ ኮንግና ሲንጋፖር )  የመሳሰሉ  ውጤታማ የልማታዊ መንግስት የካፒታል ስርዓት ህዝባቸውን ከድህነት አውጥተው ወደ ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያበቁበት ሆኖ ተመዝግቧል ፡፡

ሀገራችን ኢትዮጲያ በበኩሏ ከኒዮ-ሊበራልና ልማታዊ መንግስታት በተለየ ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ ተከትላ ቀጣይነት ያለው ፈጣንና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ ልማት ማስመዝገብ ጀምራለች፡፡

በእነዚሁ ሀገሮች መንግስት ለኢኮኖሚ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑና በግል ባለሀብቱ ሊቀርቡ የማይችሉ ምርትና አገልግሎቶችን ለህዝቡ በማቅረብ በኢኮኖሚክስቶች አገላለፅ የገበያ ክፍተትን ገበያው ይመልሰው !!  በሚል እጅን  አጣጥፎ  ሳይቀመጥ ልማትን ማፋጠን እንደሚቻል በተግባር የተፈተሸ እጅግ ፈጣን ልማት የተመዘገበባቸው ናቸው፡፡

ልማታዊና ልታዊ -ዲሞክራሲያዊ ሀገራት ማህበራዊ መሰረታቸው ወይም ጥቅሙን ለማስጠበቅ የቆሙለት የህብረተሰብ ክፍል አንደ ሊበራል ዲሞክራሲ አንድ በመቶ ብቻ  ሳይሆን 99 በመቶ ለሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ ልማታዊና ልማታዊ-ዲሞክራሲያዊ የመንግስት ባህሪ  ከኒዮ-ሊበራል የመንግስት ባህሪ የተሻለ ማህበራዊ ተቁባይነት /Social capital/  አለው ማለት ይቻላል፡፡ የታዲያ ለህዝብ ፈጣን ልማትን ከዲሞክራሲ ስርዓት ጋር ለማረጋገጥ የተሻለው መንገድ የቱ ነው? የገበያ ጉድለትን በተመረጠና በተጠና መንገድ ጣልቃ ገብቶ ኢኮኖሚን ማረጋጋት ከተቻለ፤ ፈጣንና ምዕላተ -ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ ልማት ማረጋገጥ ከተቻለ፤ ህብተረሰቡ አምኖና ፈቅዶ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የልማቱ ባለቤትና ዋና ተዋናይ በማድረግ ዲሞክራሲ -የልማት ፤ልማት ደግሞ እዚያው ሳለ ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ማረጋገጫ ማድረግ ተችሏል፡፡

የሩቅ ምስራቅ ኤሺያም ሆነ በአፍሪካ የአገራችን ተሞክሮ ይህን ያረጋግጣል፡፡  የአፍሪካ መሪዎች የሙስናና ብልሹ አሰራር መዋቅሮች  ስለሆኑ በኢኮኖሚ  ጭራሽ ጣልቃ መግባት የለባቸውም የሚለው የኒዮ ሊበራል ማደማደሚያ ከትንታኔው በላይ ጫፍ የረገጠ ስህተት ነው፡፡

የኒዮ-ሊበራል የፖለቲካል ኢኮኖሚ ስርዓት ዋነኛ አቀንቃኝ ሀገሮች ባለፉት 30 እና 40 አመታት የማምረት አቅም ቀንሶ የሰራተኛ ደመወዝ ምንም ዓይነት ጭማሬ ያልነበረበትና እንዲያውም ሰራተኛ ቅነሳ በከፍተኛ ደረጃ የተመዘገበበት እንደነበር መረጃዎች  ይገልፃሉ፡፡  በኒዮ ሊበራል ፖለቲካል ኢኮኖሚ  ህዝባዊነት የጎደለው የገበያ ስርዓት ሳቢያ የደረሰውን ማህበራዊ ውድቀት  በአንድ ተጨባጭ ማስረጃ አስደግፎ ማቅረቡ ሁኔታውን በአግባቡ ለመረዳት ያመቻል ፡፡

ለተነሳሁበት ሀሳብ ሁነኛ ማሳያ ያደረግሁት በኒዮ- ሊበራል የፖለቲካል ኢኮኖሚ ማህፀን ተፀንሶ የተወለደውና በኋላም የዚሁ የተዛባ የኢኮኖሚ መዋቅር አስተምህሮ ሁነኛ መሳሪያ ሆኖ ሌት ተቀን የሚያገለግለው የኒዮ ሊበራል ሚዲያውን ውድቀት ነው፡፡

ኒዮ- ሊበራል ሚዲያ ከልጅነት እስከ ዕውቀቱ የኒዮ- ሊበራል ማህበራዊ መሰረትን ጥቅሞች የሚያስጠብቁ ዜና፤ማስታወቂያና ዶክመንተሪወዎችን ከማሰራጨት ባለፈ የራሱን ችግሮች ዘወር ብሎ ሳያይ ረጅም የፈንጠዝያ ዘመን አሳልፏል፡፡

አሁን አሁን ግን ዘመን የተሻገሩ ችግሮቹን በማይቋቋምበት ደረጃ ሙያውንም ሆነ ባለሙያዎችን መታደግ አለመቻሉን በርካታ ምልክቶች እየታዩ ነው፡፡ እንዲያውም በዚህ ቀንና ሰዓት ብሎ መናገር ባይቻልም አንድ ቀን ግን ከነስርዓቱ ተዘርሮ ሊወድቅ እንደሚችል ታሪከና የምሁራን ጥናቶች ያስረዱናል ፡፡

እ.ኤ. አ በ2008 እና በ2009 ዓ.ም ጀምሮ የተቀሰቀሰው አለማቀፍ የገንዘብ ቀውስና በኋላም የኢኮኖሚ ማሽቆልቆል በርካታ የምዕራቡን ዓለም ታላላቅ ሚዲያ ተቋሞች ጭራ አድርጓቸዋል፡፡

እንደ እ.ኢ.አ የ2013 እና 2014 ዓ.ም የምዕራባዊያን ሚዲያዎች ሪፖርት የህትመትም ሆነ ኤሌክትሮኒክስ ጋዜጦች ህልውና የደም ስር የሆነው ማስታወቂያ ሽያጭ በነፋስ እንደሚገፈፍ ጨርቅ ዕርቃናቸውን እያስቀራቸው ነው ፤ ሲል በአሜሪካ በየአመቱ የሚታተመው ’ ዘ ስቴት ኦፍ ኒውስ ሚዲያ 2013 ‘’ የጥናት ሪፖርት እንደሚያመለከተው፡፡ በነዚሁ አመታት ታላላቅና ሰሙ-ጥር ጋዜጦች ጥንቃሬያቸው ሟሽዋል፡፡ አሁንም ባልተቋረጠ ሁኔታ ማለት ይቻላል የሚዲያዎቹ ገቢያ መቀነስ ብቻ ሳይሆን ለከፋ ኪሳራ ተዳርገዋል ሲል ያጠቃልላል ሪፖርቱ፡፡

እንደ ጥናቱ እምነት አጠቃላይ የማስታወቂያ ሽያጭ በሁሉም ኤሌክትሮኒክስና ፕሪንት ሚዲያ የጋዜጠኞች ቁጥር ከ25-30% ቀንሷል፡፡ ይህው የአሜሪካ ‘’ ዘ ስቴት ኦፍ ኒውስ ሚዲያ 2013 ‘’ ሪፖርት ጨምሮ አንደ ሚያስረዳው መረን የለሹ የኒዮ-ሊበራል ገበያ አክራሪ የኢኮኖሚ ስርዓት ምክንያት የተከሰተው የፋይናንስና አኮኖሚ ቀውስ የሚዲያ ባለሙያዎች ከሚወዱት ሙያ እነዲነጠሉ በማድረግ ረገድ የጎላ ሚና አለው ሲል አትቷል፡፡ ናሽናል ቴሌቭዥን ፤ ፐብሊክ ሰርቪስ ቴሌቭዥን የመሳሰሉትን በዋነኛነት በማስረጃ በመጥቀስ ፡፡

የኢኮኖሚ ማሽቆልቆሉን ተከትሎም ይላል ሪፖርቱ ፣ በርካታ የሚዲያ ካምፓኒዎች ልዩ ልዩ የማስተካከያ ዕርምጃዎችን እንዲወስዱ መገደዳቸውን ንና ለዚህም ወጭ መቀነስ ዋነኛው አማራጭ መሆኑን ታምኖበት ፤ ከነዚሁ የወጭ መቀነሻ

ዘዴዎች መካከል የማርኬቲንግ ፣ አስተዳደርና ማስታወቂያ ሰራተኞቻቸውን ከስራ ገበታ መቀነስ አንዱ አማራጭ አድርገው ይዘውታል ብሏል፡፡

የጋዜጠኞችን አመታዊ ጉርሻ፣ የደመወዝ ቅነሳ፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ማቋረጥ፣ ያለምንም የዲሲፕሊንና ኮንትራት ውል ሳይጠብቁ ጋዜጠኞችን ማባረር፣ እንደ መፍትሄ ተወስዶ እየተሰራበት መሆኑም የሪፖርቱ አካል ሆኖ ተካቷል ፡፡ የጋዜጠኞች የክብረ-በዓል የህክምና ፈቃድ ይከፈል የነበረው ወጭ ሙሉ በሙሉ ተከልክሏል፡፡

ሪፖርቱ ጨምሮ እንደሚያስረዳው በርካታ የኤሌክትሮኒክስም ሆነ ህትመት ተቋሞች የጋዜጠኞቻቸውን ቁጥር በ50% ቀንሰዋል፡፡ የጋዜጠኞች ደመወዝ ከአመት አመት ማሽቆልቆልና ፣ ሰራተኛ ማባረር የተለመደ የዕለት ተዕለት ተግባር ሆኗል ፣ በምዕራባዊያን ሚዲያ ካምፓኒዎች ዘንድ፡፡ ሚዲያ ካምፓኒዎች የትራንስፖርት ወጭ ለመቀነስ ሲባል ሽፋን የሚሰጡበትን አካባቢም በብዙ ኪ.ሜትር ቀንሰዋል፡፡

በኢኮኖሚው ማሽቆልቆል ምክናያት የሚዲያ ካምፓኒዎች የማስታወቂያ ሽያጭ በመቀነሱ ምንም የፕሮግራም ለውጥ ሳያደርጉ ሰራተኛና የሰራተኛ ጥቅማጥቅም በእጅጉ ቀንሰዋል፡፡ የሚዲያ ሳንባ ተደርገው ይቆጠሩ የነበሩት የምርትና አገልግሎት ካምፓኒዎች በመዘጋታቸውና ድንበር ተሻጋሪ ገበያ ሽቀጣ ሽቀጣቸው መቆሙ የምዕራባዊያን ሚዲያዎችን ለሁነኛ ቀውስ ዳርጓቸዋል ፡፡

ታዋቂው ኒውዮርክ ታይምስ ከ ሜክሲኳዊው ቢሊየነር ካርሎስ ሰሊም 250 ሚሊዮን ዶላር የአደጋ ጊዜ ብድር ተደጉሟል፡፡ ይህንኑ የጋዜጣ ካምፓኒ ለማገዝ ወይ ለመደገፍ ካርሎስ ስሊም ለኒውዮርክ ታይምስ እ ኤ አ በ2009 ከላይ የተጠቀሰውን ያህል ገንዘብ ደጉሟል፡፡

ከዓለማቀፉ የገንዘብ ቀውስና ኢኮኖሚ ማሽቆልቆል አደጋ ወዲህ በአሜሪካ ብቻ 10 ሺ የሚደርሱ ጋዜጦች በራቸውን ቆልፈው ጋዜጠኞችን ከሚወዱት ስራ አሰናብተዋል ፡፡ በ2000 ዓ.ም አውሮፓ ታዋቂ ኒውስ ሩሞች የጋዜጠኞቻቸውን ቁጥር በ30 % ቀንሰዋል ፡፡ ( Posen stil & Mitchell 2011) በዚህም ምክንያት የምዕራባዊያን ኒዮ ሊበራል የሚዲ ኢንድስትሪ አደጋ ላይ ነው፣ ማለት ይቻላል፡፡

ሪፖርቱ ጨምሮ እንደሚያስረዳው የምዕራባዊያን ሚዲያዎች እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር 2012 የዘገባ አቅማቸው እጅግ ቀንሶ የታየበት አመት የለም፡፡ የሚዲያ ኢንዱስትሪው ከሁለት አመት በፊት ማለትም በ2000 ከነበረበት 30 በመቶ የቀነሰ ነበር፡፡

በኬብል ቻናል በምርምር ዘጋቢነቱ የሚታወቀው ሲ.ኤን.ኤን እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ከ2007 --- 2012 ባሉት ዓመታት ከሚያዘጋጃቸው የምርምር ዘገባ ሪፖርት ፓኬጆችን በግማሽ ቀንሷል፡፡

ታይም ማጋዚን በአሁኑ ሰዓት ብቸኛ የህትመት ሳምንታዊ ዜና አቅራቢ ሆኗል፡፡ ያም ሆኖ ከሰራተኞቹ 50 በመቶ በ2013 መጀመሪያዎቹ ወራት አሰናብቷል፡፡ የአፍሮ አሜሪካ ዜና ተቋም የሆነው ችካጎ ዲፈንደር የኢዲቶሪያል ስታፍ ቁጥር በአራት ዕጥፍ ቀንሷል፡፡ ከ28-32 የነበረው የህትመት ገፅ ብዛትም በ2008 ከነበረው ከ2012 ወዲህ ወደ 16-20 ገፅ ብቻ ይዞ መውጣት ጀምሯል፡፡

የአለም ቱጃሮችን የሀብት መጠንና ስም ዝርዝር በመዘገብ የሚታወቀው ፎርብስ መፅሄት መረጃ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው የሚዘግቡ ባለሙያዎችን ቁጥር በእጅጉ ቀንሶ የቱጃሮችን ሀብት ማቆሚያ በሌለው '' ምክንያትና ውጤት '' ላይ ተመስርቶ የመዘገብ ሳይንስ / algorism/ እየተጠቀመ ስለመሆኑ / The State of News Media 2013 / ዘግቧል ::

የአውሮፓና አሜሪካ የሚዲያ ተቋማትና ጋዜጠኞች ከ2008 ጀምሮ የተከሰተውን የፋይናንስና ኢኮኖሚ ቀውስ ተከትለው የመዋቅርና የሰው ሀይል ቅነሳ ስራቸውን አጠናቅረው ቀጥለዋል ፡፡ እንደ ( ስፔን) ዓይነት ቀውሱ የበረታባቸው ሀገር ጋዜጠኞች በ2012 ሚዲትራንያንን ባህር አቋርጠው ሰሜን አፍሪካ (ሞሮኮ) የኩሽና ሰራተኛ እስከመሆን ሲደርሱ ሊበራል ኢኮኖሚው ግን ፣ ሊታደጋቸው አልቻለም፡፡ (ETV. News ፡ 2005)

ኒዮ-ሊበራል ኢኮኖሚና በስሩ የተዋቀረው ገበያ አክራሪ ጥገኛ ሚዲያው ዳገት መውጣት በተሳነበት በአሁኑ ሰዓት በአፍሪቃ በልማታዊና ልማታዊ- ዲሞክራሲያዊ መንገድ ፈጣንና ዘላቂ ልማት እየተመዘገበ ይገኛል፡፡ የአዲሶቹና ልማታዊና ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስታት አማራጭ የካፒታል ስርዓት ተከትለው ያስመዘገቡትን ዲሞክራሲና ፈጣን ዕድገት በአዲስ ጉልበት ለዓለም ማሳየት የሚችል እንደ/ CCTV. Africa/ ዓይነት ሚዲያ ወሳኝ ነው፡፡

ለልማታዊና ዲሞክራሲያዊ ጎዳና አንደበት የሚሆን ከኒዮ -ሊበራል ተፅዕኖ ነፃ የሆነ መገናኛ ብዙሀን ማስፈለጉ አንድ ነገር ሆኖ ዓለማዊ ሁኔታችን ከአንድ አማራጭ ወደ ብዙ አማራጮች ሽግሽግ እያተደረገ ስለመሆኑ አገራችን አንዷ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በተመረጡ የኢኮኖሚ ሴክተሮች የመንግስትን ጣልቃ ገብነት ለዘመናት ሲኮንን የነበሩት የእነ ጆርጅ ቡሽ አስተዳደር ሳይቀር ከፋይናንስ ስርዓት ቀውሱና ኢኮኖሚ ድቀቱ በኋላ ፣ ግለ-ሂስ የወሰዱበትና ራሳቸውን ሲዋሹ እንደነበር የገለፁበት ሁኔታ እንዳለ መረዳት ተችሏል፡፡

የኒዮ -ሊበራል ፖለቲካል ኢኮኖሚ ሲስተም ሀይሉ ሙሉ በሙሉ ወርዷል ባይባልም እንኳ ቢያንስ ብቸኛ እንዳልሆነና አማራጭ የካፒታል ሲስተም እንዳለው የተጋለጡበት ሁኔታ መፈጠሩን አለም ቀደም ሲልም አበክሮ ተናግሯል፤ አሁንም በተግባር እየተረጋገጠ ነው፡፡

ታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ በ1994 ዓ.ም አንድ የአገር ውስጥ ጋዜጠኛ ላነሳላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ሀሳቤን ማጠቃለል ወደድሁ፡፡ ታላቁ መሪ ‘ የደርግን ያህል ግዙፍና እስካፍንጫው የታጠቀ የአምባገነን መንግስትና ግዙፍ ሰራዊት ኢህአዴግ እንዴት ሊያሸንፍ ቻላ ? በሚል ከጋዜጠኛው ለቀረበላቸው ጥያቄ በሚከተለው መንገድ መመለሳቸውን አስታውሳለሁ፡፡

‘’ብዙ መሳሪያና ወታደራዊ ሀይል ይዞ ለፍልሚያ ከመነሳት ይልቅ ፤ ቀና ሀሳብ ይዞ መነሳት የተሻለ መሆኑን በህይወት ዘመኔ አረጋግጫለሁ ፡፡ ያ ! ቀና አስተሳሰብ ህዝባዊ ድጋፍ አመጣና ለድል በቃን ማለቱ ይቀላል፤ ስለዚህ ቀና አስተሳሰብ ሀይል ነው’’ ሲሉ ገልፀዋል፡፡

በምዕራባዊያን አጠራር አፍሪቃ ጨለማ አህጉር ነች፡፡ በኒዮ-ሊበራል ፖለቲካል ኢኮኖሚ ድምዳሜ የአፍረቃ መንግስታት መዋቅር የሌባና ሙሰኛ ቡድን ስለሆነ ኢኮኖሚውን ለገበያና ገበያ ብቻ ከመጣል ባሻገር በኢኮኖሚው ጣልቃ አይግቡ፡፡ ወዘተ…በመሳሰሉ ከትንታኔዎች በላይ ድምዳሚያቸው የተሳሰቱ የኒዮ-ሊበራል ምሁራንና ፖለቲከኞች የተወሰነባት አህጉር ነበረች፡፡

ኢትዮጺያ ህዝብና መንግስት ግን ለኒዮ- ሊበራል ጫፍ የረገጠ ማደማደሚያ ሳይበገር የገበያ ክፍተትን ገበያው ይመልሰው !! በሚል እጅን አጣጥፎ ሳይቀመጥ ለኢኮኖሚ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑና በግል ባለሀብቱ ሊቀርቡ የማይችሉ ምርትና አገልግሎቶችን ለህዝቡ በማቅረብ ፤ የሌባ መዋቅር ሳይሆን ልማትን የሞት ሽረት ጉዳይ ያደረገ መንግስታዊ መዋቅር በመምራት ፤ ዲሞክራሲ እንደ ኒዮ ሊበራል ከልማት በኋላ የሚመጣ ቅጥያ ወይም የቅንጦት ዕቃ ሳይሆን ከልማት የማይነጣጠል ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መስመር በመከተል ፤ ቀጣይነት ያለው ፈጣንና ህብረተሰቡን በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ ባለሁት አህዝ ልማት እያስመዘገቡ ናቸው፡፡

እንደ ኒዮ ሊበራል ድምዳሜ አፍሪቃ የጨለማ አህጉር ሳትሆን ፤ በአዲሱ ሚሊነየም ታላቅ ታሪካዊ ክንውን የሚፈፀምባት አህጉር እንድትሆን ኢትዮጺያ የመሪነት ሚና በመጫወት ላይ መሆኗን በዓይናችን እያየን እንገኛለን ፡፡

ዓለማችን ከብቸኛ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ዋልታ ወደ ባለ ብዙ የፖለቲካና ኢኮኖሚ አማራጮች ከአንድ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ልዕለ-ሀያል ወደ ባለ ብዙ ዋልታ በሽግግር ላይ ነች፡፡ የሀገራችን ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መስመር አንድ ማሳያ ነው፡፡ ሀያል መስመራችንን ጠብቀን የህዳሴ ጉዟችንን እናሳካ !!